የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ (ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር፣) መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

ቁ. 60

21.11.69

የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ሕብረትና የድርጊት ፕሮግራሙ

ከዚህ ጋር ተያይዞ ለሰፊው ሕዝብ ድምፅ አንባቢያች የቀረበው "የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ሕብረት የድርጊት ፕሮግራም" በኅብረት ኮሚቴው 30ኛ ስብሰባ ላይ፣ ሐምሌ 12 ቀን 1969 ተነበና ታርሞ የፀደቀ ፕሮግራም ነው:: እያንዳንዱ ድርጅት የራሱን መግቢያ ጽፎ ፕሮግራሙን በሰፊው እንዲሰራጭ የተወሰነውም በዚሁ በ30ኛው ስብሰባ ላይ ነው:: አንባቢ እንግዲህ ካሁኑ "የትኛው የኅብረት ኮሚቴ" የምን 30ኛ ስብሰባ ?" ብሎ ጥያቄያችን እንደሚያቀርብ ምንም ጥርጥር የለውም::

እንደሚታወቀው ባለፈው የካቲት ወር 1969 ፣ አምስት ሕቡእ ድርጅቶች—ማለትም የመላ ኢትዮጵያ ሶሺያሊስት ንቅናቄ/መኢሶን/፣ የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል /ኢጭአት/ ፣ የወዛደር ሊግ/ሊግ/፣ አብዮታዊ ሰደድ/ሰደድ/፣ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሪቮሉሺናዊ ድርጅት/ማሌሪድ/፣—አንድ የጋራ መግለጫና ማርሃ ግብር አውጥተው አሠራጭተው ነበር:: ከዚያን ጊዜ ወዲህ ሕቡእ ድርጅቶችም በየልሳኖቻቸው፣ እንደዚሁም የተለያዩ አብዮታዊ ግለሰቦችና ቡድኖች በመንግሥት የዜና ማዘራጫ መሣሪያዎች፣ ደግመው ደጋግመው የተራማጆችን ኅብረት መጠንከር ጠይቀዋል:: በተለይም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ አንዳንድ የጥናት ቡድኖችና ግለሰብ ፀሐፊዎች፣ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የጠላት ሰፈር እንዴት እንደተባበረ ከገለጹ በኋላ የወዳጁ ሰፈር፣ ይልቁንም ደግሞ የኢትዮጵያ ተራማጅና ማርክሲስት—ሌኒንስት ቡድኖች ለምን ባፋጣኝ እንደማይተባበሩ፣ ለምን የየካቲት የጋራ መግለጫና መርሃ ግብር በተግባር ተተርጉሞ እንደማይታይ፣ ቅሬታ በሞላበት አነጋገር ደጋግመው ጠይቀዋል:: "የኢትዮጵያ ተራማጆች ተባብረዋል ይባላል፣ ምን ሠሩ?" የሚለው ጥያቄ በየእለቱ ያጋጥማል:: የዚህ ዓይነቱን ጥያቄ የሚያቀርቡና በሐቅ ለአብዮቱ ሰፈር መጠናከር የሚቆሙ፣ ለአብዮቱ የወደፊት እድል የሚጨነቁና የየበኩላቸውንም አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚጓጉ ጓዶች ሁሉ፣ የኅብረት ኮሚቴ የሚባል ነገር እንዳለና ይህም ኮሚቴ እስከዛሬ ድረስ 30 ጊዜ የተሰበሰበ መሆኑን ማወቃቸው እጅግ በጣም ያጠራጥራል:: ለነዚህ ጓዶች ለመኢሶን አባላትና ደጋፊዎች፣ እንደዚሁም ባጠቃላይ ለሰፊው ሕዝብ፣ ኅብረቱ ከየት ተነስቶ አሁን ከምን ላይ እንደደረሰ የሚገለጽበት ወቅት አሁን መጥቷል ብለን እንገምታለን:: የዚህ ዓይነቱ ገለጻ ቢደረግ፣ አንዳንድ ሐቀኛ ጓዶች ከዜና ማጣት የተነሳ የሚያቀርቡትን ሂስና የሚሰማቸውን ቅሬታ ምናልባት ይቀንስ ይሆናል::

የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች ኅብረት የተቋቋመው ከረጅም ጊዜ ፖለቲካዊና ርዕዮታለማዊ ትግል በኋላ እንጂ ባለፈው የካቲት ወር የጋራ መግለጫው በወጣበት ጊዜ ድንገት የተፈጠረ አይደለም:: በኅብረቱ ትግል ድርጅቶች መካከል፣ ከዛሬ ዓመት ገደማ ጀምሮ ረዘም ያሉ የሁለት ወገን/ባይላተራል/ ውይይቶች ተካሂደዋል:: አንዳንዶች ድርጅቶች፣ ለምሳሌ መኢሶንና ሊግ፣ በጽሑፎቻቸውም ጭምር ሃሳቦች ተለዋውጠዋል፣ ክርክሮችም አካሂደዋል::

የዚህ ዓይነቱ የርስ በርስ ውይይት ለስምንት ወራት ያህል ከተካሄደ በኋላ ባለፈው ጥር 24 ቀን 1969፣ ማለትም ከጥር 22ቱ የሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ቋሚ ሰልፍ በኋላና ለጊዜው ነግሰው የነበረት እነዓለማየሁ ኃይሌ ከመወገዳቸው ሁለት ቀን አስቀድሞ የአምስቱ ድርጅቶች ወኪሎች የተገኙበት የመጀመሪያው የኅብረት ስብሰባ ተደረገ:: ምንም እንኳ በትክክል ውይይት ተደርጎበት ስም ባይሰጠውም፣ "የኅብረት ኮሚቴ" በመባል የታወቀው አካል በዚህ ዕለት፣ ካንዱ ድርጅት በስተቀር የቀሩት ሁለት ሁለት ጓዶችን የወከሉበት የዘጠኝ አባላት ጉባኤ ነው:: በግንቦት 20 ቀን 1969፣ በ18ኛው የኮሚቴው ስብሰባ ላይ ፣ እያንዳንዱ ድርጅት ሶስት ሶስት ጓዶችን በመወከል፣ ኮሚቴው እንዲሰፋ ተደርጎ ፣ አሁን አሥራአምስት አባላትን ይዟል::

እንደተገለው የመጀመሪያው የኅብረት ስብሰባ የተካሄደው በጥር 24 ቀን ሲሆን፣ የኮሚቴው ሥራ በማያቋርጥ አኳኋን ቀጥሎ ፣ በስምንተኛው ስብሰባ፣ የካቲት 18 ቀን 1969 የጋራ መግለጫውንና መርሃ ግብሩን ኮሚቴው አፀደቀ:: እነዚህ ሰነዶች በየድርጅቱ ተባዝተው ተሰራጩ:: ከጥር 24 እስከ የካቲት 18 ድረስ ፣ በሶስት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ በና አቆጣጠር ስምንት ስብሰባዎች ሲካሄዱ፣ ከየካቲት 18 እስከ ሚያዝያ 10 ድረስ ግን ማለትም በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ፣ የተካሄዱት ስብሰባዎች ሁለት ብቻ ናቸው!! ከዚያም እንደገና ለሶስት ሳምንታት ያህል ምንም ስብሰባ ሳይኖር ቆይቶ፣ አሥራ ሁለተኛው ስብሰባ

ግንቦት 10 ቀን ይደረግና እስከወሩ መጨረሻ ድረስ አሥራ ሁለት ሌሎች ስብሰባዎች ይካሄዳሉ:: በሰኔ ወር አንድም ስብሰባ ሳይኖር ይቀርና፣ አሁን ከሐምሌ 1 ጀምሮ ደግሞ በተፋጠነ ሁኔታ ስብሰባው በመቀጠል ላይ ይገኛል::

የጋራ መግለጫውና መርሃግብሩ ከፀደቀ በኋላ፣ ወዲያውኑ የተጀመረው ሥራ የኅብረቱን የመተዳደሪያ ደምብ ማርቀቅ ነበር:: ይህ ደንብ ረቂቅ ለአንድ ወር ተኩል ያህል እንደዚሁ ከተቀመጠ በኋላ፣ የመጀመሪያው ውይይት የተከፈተበት ሚያዝያ 18 ቀን 1969 ነበር:: በግንቦት ወር የተካሄዱት አሥራ ስድስት ስብሰባዎች የፈጁት ይህን ያህልም በደንቡ ላይ ለመከራከር ሳይሆን ፣ በየካቲት 18 ቀን በጋራ ማግለጫው ውስጥ በጸደቁት የውይይትና የስምምነት ነጥቦች ላይ እንደገና በመከራከር ነበር!!

ይህ የቀኖቹና የስብሰባዎች ቁጥር ድርደራ አንባቢውን እንደሚያሰለች ብናውቅም፣ እነዚህ የጠቀስናቸው ከነርሱ ብቻ እንኳን በመነሳት ፣ አንባቢ ሁለት ቁምነገሮችን ለመገንዘብ እንደሚችል በማመን ነው:: እነዚህም፣ አንደኛ፣ በሕብረቱ አባል ድርጅቶች መካከል በተካሄዱት ውይይቶች ውስጥ ፣ በሥራ ብዛት የመገናኛ ጊዜ መጥፋቱ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊ ችግሮችም እንደነበሩና፣ ሁለተኛ፣ እንደዚያም ሆኖ ግን፣ ለሰፊው ሕዝብ በዝርዝር ያልተገለጹና በፖለቲካዊ ይዘታቸው በጣም የዳበሩ ውይይቶች እንደተካሄዱ ነው:: ጊዜውና ሁኔታው ፈቅደው በዚህ በኩል ያለው ስነጽሑፍ በይፋ በሚወጣበት ወቅት ሰፊው ሕዝብ በቀጥታ መንገድ ዲያሌክቲክን የመደብ ትግልን ያጠናበታል ብለን እናምናለን:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ በሃቀና በአብዮታዊ መንፈስ ተገፋፍተው ፣ በአዲስ ዘመን ላይ በየጊዜው ስለተራማጆች ኅብረት ፣ ስለውህደት ፣ ስለወዛደሩ ፓርቲ፣ ስለሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ...ወዘተ አስፈላጊነት በመቆርቆርና አንዳንዴም በምሬት የሚጽፉት ጓዶችና የጥናት ቡድኖች ይህንን ሥነ ጽሑፍ ቢያገኙ ኖሮ ስላሉት ችግሮች ምንና በተገነዘቡና የየበኩላቸውንም አስተዋጽኦ ምንና ባበረከቱ ነበር!!

ከጥር 24 ጀምሮ እስከዛሬ ፣ ማለትም ከዚህ ጋር የተያያዘው የኅብረቱ የድርጊት ፕሮግራም እስከፀደቀበት 30ኛው ስብሰባ ድረስ ፣ ፈረንጆች እንደሚሉት ሁሉ፣ በድልድዩ ሥር ብዙ ውሃ አልፎአል:: ብዙ ነገሮች ተለዋውጠዋል:: ከጥር 24 በኋላ ፣ በጥር 26 የነዓለማየሁ ኃይሌ መወገድ ከዚያም የአብዮቱ ከተከላካይነት ወደአጥቂነት መሸጋገር፣ እንደገናም በአብዮት ሰፈር ውስጥ የውንብድና መስፈንና የፀረ አብዮቱ ሰፈር መጠናከር ተፈራርቀው መጥተዋል:: የኢትዮጵያን ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች፣ የኅብረቱን ድርጅቶች በሚመለከተውም በኩል፣ የጠበቀ መቀራረብና ደግሞም መራራቅ፣ ጓዳዊ ትብብርና ደግሞም የርስበርስ ሹኩቻ ፣ አብዮታዊ ያንድነት መንፈስና ደግሞም ከፋፍ አርስ በርስ የመጠራጠርና፣ በኅብረቱም ውስጥ በልዩ ልዩ ነጥቦች ላይ የየድርጅቱ የአሰላለፍ ለውጦች ታይተዋል:: እንግዲህ አሁን ያለንበት ደረጃ የመቀራረብና አገሪቷንና አብዮቱን እየከበቡና እየበረበሩ ሁኔታውን ለቀልበሳ በሚያመቻቹት ኃይሎች ላይ በጋራ የመሰለፊያ ደረጃ ነው:: የሕብረቱ የድርጊት ፕሮግራም ይህንን ተግባር ለማከናወን እንዲያስችለን የታቀደ ሲሆን ወደፕሮግራሙ ይዘት ከማለፋችን በፊት አንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮችን በቅድሚያ ማንሳት ያስፈልጋል ብለን እናምናለን::

1. የቆዩ የውይይት ነጥቦች

ከሕብረቱ የመጀመሪያ ስብሰባ ፣ ማለትም ከጥር 24 በፊትም ቢሆን፣ መኢሶን ከሕብረቱ አባል ድርጅቶች ጋር ለስምንት ወራት ያህል ውስጥ ያካሄዳቸው ውይይቶች የሚመለከታቸው ነጥቦች በየካቲት የጋራ መግለጫ ውስጥ ከወጡት ነጥቦች የተለዩ አይደሉም:: እነዚህም የኢትዮጵያ አብዮት መሠረታዊ ጥያቄዎች የሆኑት፣ የጊዜው ሁኔታ ትንተና፣ የሥልጣን አያያዝ ጥያቄ፣ የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ፣ የብሔረሰቦች ጥያቄ፣ ስለኢትዮጵያ መለዮ ለባሽና ሕዝባዊ ጦር ስለሚመሠረትበት ሁኔታ፣ ስለወዛደሩ ፓርቲ አመሠራረት ናቸው:: በዚህ ነጥቦች ላይ በሕብረቱ ከሚቴው ውስጥም ሆነ ከዚያ በፊት ተደጋግሞ ውይይት የተደረገው ፣ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች የመኢሶንን አቋም ቀደም ብለው ስላላወቁት ሳይሆን፣ ወይንም አባል ድርጅቶቹ የመኢሶንን ፕሮግራም ስላላነበቡትና የሰፊው ሕዝብ ድምፅን ይዘቶች ስላልተከታተሉ ሳይሆን፣ ባንድ በኩል በነዚህ ነጥቦች ላይ ሙሉ መግባባት እንዲኖርና በሌላ በኩል ደግሞ ልዩነቶቻችን ካሉ እነርሱን የምናስወግድበትን መንገድ በጋራ ለመቀየስ እንድንችል ነበር::

በነዚህ መሠረታዊ የኢትዮጵያ አብዮት ጥያቄዎች ላይ፣ በየካቲት ወር በወጣው የጋራ መግለጫ ውስጥ የየድርጅቱ አቋም፣ ባንድ ነጥብ፣ ማለትም በብሔረሰቦች ጥያቄ ላይ እንኳ በሌላው ሁሉ ላይ አንድ እንደሆነ ተገልጿል:: የኢትዮጵያን ኅብረተሰብ ዋና ዋና ቅራኔዎችና የጊዜውን ሁኔታ በሚመለከተው በኩል አንድ ዓይነት አስተያየት ነበረን:: የወዛደሩን ፓርቲ አመሠራረት በሚመለከተው በኩል፣ "በኢትዮጵያ ሁኔታ አሁን በህቡዕ የሚታገሉት ማርክሳዊ ሌኒናዊ ቡድኖችና ሌሎችም በትግሉ ውስጥ የሚፈጠሩ ቡድኖች ተዋሀደው እንጂ አንድ ድርጅት ብቻውን ተስፋፍቶና አሔጐ ወይም ደግሞ ከውስጡ ፀረ ወዛደር የሆኑ ኃይሎችን አጽድቶ ብቻውን ወደወዛደር ፓርቲነት የሚለወጥበት ሁኔታ የለም" በሚለው ላይ ተስማምተው ነበር:: ምንም እንኳ መኢሶን ስለወዛደር ፓርቲ አፈጣጠር የተባለውን "የውህደት ቲዎሪ" ያቀረበው ከማንኛውም ድርጅት በፊት በየካቲት 1967 መሆኑን በፕሮግራሙም

ውስጥ ይኸው ነገር በግልጽ እንደሰፈረ፣ እንደዚሁም ድርጅታችን ለተራማጆች ሕብረት ደጋግሞ ጥሪ እንዳደረገ ቢታወቅም፣ በዚያን ጊዜ የዚህ ዓረፍተነገር ሁለተኛ ክፍል የቱጨመረው፣ በአንዳንድ የሕብረቱ ድርጅቶች በኩል መኢሶን ብቻውን ወደርዛደር ፓርቲ ለመለወጥ ይፈልጋል የሚል ጥርጣሬ ስለነበረ ነው:: ይሁንናም፣ ከጋራ መግለጫው ወዲህ ከነበሩት ሁኔታዎች ና ከተካሄዱት ውይይቶች እንደሚታየው ሁሉ፣ መኢሶን ቢምልና ቢገዘትም፣ ስለዚሁ ጉዳይ ደጋግሞ ቢጽፍም፣ በተግባርም ለሕብረትና ለውህደት የሚታገል መሆኑን ቢያሳይም፣ ጥርጣሬው ፈጽሞ ሊወገድ ባለመቻሉ፣ባንዳንድ አካባቢዎች በስበብ በአስባቡ በዚሁ ጥያቄ ላይ ዘመቻዎች ተካሄደውብናል::

የዲሞክራሲያዊ መብቶችን ጥያቄ በሚመለከተው በኩል ፣የድርጅታችን አቋም ብቻ ሳይሆን የሌሎቹም ድርጅቶች አቋሞች በየጽሑፎቻቸው ተደጋግመው ተገልጸዋል:: ሁሉም "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ" የሚለውን መፈክር፣ በሞሳ ጉደል ከተፈጠረበት ቀን ጀምሮ ለማለት ይቻላል፣ሲያስተጋቡት ቆይተዋል:: በጋራ መግለጫውም ውስጥ የሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል፣—

> "......በአሁኑ ወቅት አብዮቱን ለመቀልበስ ያሰፈሰፉትን አድሃሪያን በይበልጥ ለመቋቋም በሰውር ታፍነው የሚሰሩ ተራማጅ ድርጅቶች ትግላቸውን በይፋ ለማካሄድ እንዲችሉና በተለይ ደግሞ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ለመመሥረት የሚያስችሉትን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲያችና ሰፋፊ ድርጅቶች ለማቋቋም እንዲችሉ ባስቸኳይ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ መታወጅ አለባቸው:: ለዚህም የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች የጋራ ትግል ያደርጋሉ::"

ይህ አቋም ፍጹም አብዮታዊ እንደሆነና የኢትዮጵያን ሕዝቦች የጊዜውን አጣዳፊ ጥያቄ እንደሚያስተጋባ ግልጽ ስለሆነ ፣መኢሶን በዚህ የጋራ አቋም ላይ ሲፀና አንዳንድ የሕብረቱ ድርጅቶች ግን ማፈግፈግ የጀመሩ ይመስላል::ይህንን ከዚህ በታች እንመለስበታለን::

የመንግሥትን ሥልጣን በሚመለከተውም በኩል፣ የየካቲት የጋራ መግለጫ ፍጹም ማርክሳዊ ሌኒናዊ የሆነ አቋምን ያዘለ ስለሆነ፣ መኢሶን ቀደምም ዛሬም በዚያን አቋም ላይ ጸንቷል:: የመንግሥትን ሥልጣን መያዝ ያለበትና የሚችለም አንድ ድርጅት ወይም ቡድን ሳይሆን የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ሰፊ ሕዝብ ነው:: የነቃ፣ የተደራጀ፣ የታጠቀ ሰፊ ሕዝብ ማለት ደግሞ ማርክሲዝም ሌኒንዝም የሚመራ የወዛደር ፓርቲና በዚህ ፓርቲ አመራር ስር የቆመ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባርና ሕዝባዊ አብዮታዊ ጦር ያሉት ሕዝብ ማለት ነው:: እነዚህ ሶስት መሣሪያዎች እስከሌሉት ድረስ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ፊውዳሊዝምን፣ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ሊደመስስ አይችልም::እነዚህን ሶስት ጠላቶች ካልደመሰሰ ደግሞ የመንግሥትን ሥልጣን ለመያዝ ፣ለመደላደልና አዲስ ኅብረተሰብን ለመገንባት ፈጽሞ አይችልም:: ድርጅታችን ለዚህ ዓይነቱ የሕዝብ ሥልጣን እንደሚታገልና ይህም ትግል ደግሞ የረጅም ጊዜ መራራ ትግል እንደሚሆን ዛሬ ሳይሆን ገና በጨለማው የኃይለሥላሴ ዘመን አምኖበት ሰፊውን ሕዝብ ሲቀሰቅስበት የኖረ የፖለቲካ መስመር ነው:: ይሁንናም፣ የቀኝም ሆኑ የግራ የመኢሶን ተቃዋሚዎች ይህንን የድርጅታችንን አቋም እያጣመሙ፣ ነጩን ጥቁር፣ ጥቁሩን ነጭ እያሉ ፣ለማንም ሀቀኛ ተመልካች ግልጽ የሆነውን ነገር በአሉባልታቸውም እየሸፋፈኑ ፣ መኢሶን ባቋራጭ ሥልጣን ለመያዝ ይፈልጋል በማለት በኛና በሌሎች ተራማጅ ድርጅቶች መካከል ጥርጣሬን ለመፍጠር ሲፍጨረጨሩ ቆይተዋል፤ እየተፍጨረጨሩም ናቸው::

የኢትዮጵያን መለዮ ለባሽና የወደፊቱን ሕዝባዊ አብዮታዊ ጦር አመሠራረት በሚመለከተውም በኩል በጋራ መግለጫው ውስጥ በሰፈረው ነጥብ ሙሉ በሙሉ እናምንበታለን:: "...ይህንን ሕዝባዊ አብዮታዊ ጦር ከወዛደሩ፣አርሶአደሩ፣ ከሌሎች ተራማጅ ኃይሎችና አሁን ካለው መለዮ ለባሽ ለአብዮቱ ከሚቆመው ወገን ማቋቋም የሚቻልበት ሁኔታ አለ::" ይላል መግለጫው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ የቀረበው የድርጊት ፕሮግራምም በመሠረቱ ይህንን አስተሳሰብ የሚያስተጋባ ሲሆን፣ ከየካቲት ወዲህ ሕዝባዊ ሠራዊት፣ ማለትም ከአርሶአደሩ የመነጨ ሠራዊት ስለተገነባ፣ የወደፊቱ ሕዝባዊ አብዮታዊ ጦር ከዚህኛውም ኃይል እንደሚያገኝ ይታመናል::ሕዝባዊ አብዮታዊ ጦር እንደመሠረት ለማድረግ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች አንዱ የሶሻሊዝምን ርእዮተዓለም በመደበኛው መለዮለባሽና በሕዝባዊ ሠራዊቱ ውስጥ በሰፊው ማስገባት ነው:: ስለሆነም፣ እንደሌሎች ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ሁሉ፣ መኢሶንም ለዚሁ መታገል ይቀጥላል::

በሕብረቱ አባል ድርጅቶች መካከል ሙሉ ስምምነት ያልተደረሰበት አንድ ነጥብ ቢኖር፣ እርሱም የብሔረሰብ ጥያቄ ነው:: በጋራ መግለጫዉ ውስጥ እንደተጠቀሰው ሁሉ፣ "በዚህ ጥያቄ ላይ ለወደፊቱ ሰፊ የሆነ ውይይትና ክርክር ለማድረግና ወደጋራ አቋም ለመድረስ ቡድኖቹ ተስማምተዋል::" የሁንናም ፣ ውይይቱ ገና በሙገባ ጀምሯል ለማለት በማይቻልበት ሁኔታ፣ ይህ ጥያቄ በመኢሶን ላይ ዘመቻ ከሚካሄድባቸው ነጥቦች አንዱ ሆኖ ቆይቷል:: እንመለስበታለን::

የወዛደር ፓርቲ አመሠራረት፣የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ ፣የመንግሥት ሥልጣን ጉዳይ ፣..ወዘተ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ነጥቦች በሙሉ፣ የቀዱ የውይይት ነጥቦች ናቸው:: ባለፈው ዓመት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ሊታወጅ ሰሞን ሲታይ በነበረው የዲሞክራሲ ሽርታ ፣እነአዲስ ዘመን በሃያ አምስት ባንቆና ለዚ

ያውም በስንት ሽሚያ ይሸጡ በነበረበት ወቅት፣ እንኳንስ ሕቡእ ድርጅቶች ቁርተው ያልተደራጀውም ሰፊ ሕዝብ ቢሆን ፣ ከነዚህ የውይይት ነጥቦች በተሳልቆቹ ላይ ሰፊ ክርክር አካሄዷል::

ይሁንናም፣ እነዚህን የቀዱ የውይይት ነጥቦች የጋራ መግለጫው ለመጨረሻ ጊዜ አከራካሪ ያደርጋቸውና ከዚያም ሁሉም ድርጅት ይበልጥ እርስ በርስ ከሚተማመንበት ደረጃ ላይ ይደርሳል ተብሎ ሲጠበቅ፣ ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ ፣ መግለጫው ወጥቶ በሰስተኛው ወሬ ነጥቦቹ እንደገና ለውይይት እስከመቅረብ ደርሰዋል:: ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት በነዚህ ነጥቦች ላይ የያንዳንዱ ድርጅት አቋም ግልጽ ሳይሆን መቅረቱ ሳይሆን፣ በድርጅቶቹ መካከል የመጠራጠር መንፈስ ሊጠፋ ባለመቻሉ ነው :: መኢሶን በልዩ ልዩ እትሞቹ ደጋግሞ እንደገለጸው ሁሉ፣ ይህ ጥርጣሬ ሊጠፋ ያልቻለው ኅብረተሰባችን ገና ከፊውዳሳዊው ስርአት የአስተሳሰብ ዘዴዎች ባለመላቀቁና ዲሞክራሲያዊ መብቶችም ሆኑ ዲሞክራሲያዊ ያስተሳሰብና ያሰራር ዘዴዎች በፍጹም ያልተለመዱ በመሆናቸው ነው:: በዚህ ዓይነቱ ኅብረተሰብ ውስጥ ሰዎች ያንዱን ድርጅት ዓላማ "የሚገምቱት" በቀጥታ መንገድ ድርጅቱ በወሰደው ግልጽ አቋምና በቀጥታም መንገድ በሚሠራው፣ ማንም በቀላሉ ሊያየው በሚችለው እንደፀሐይ በጠራ ድርጊቱ ሳይሆን ፣ ሰዎች በሚያወሩት አሉባልታ፣ በሐሜት፣ በተንኮለኞች የነገር ሸረባ ላይ ተመስርተው ነው:: እነዚህ "የመገመቻ" ዘዴዎች ደግሞ ከሳይንሳዊ ያመለካከትና ያሰራር ዘዴዎች፣ ከዲያሌክቲካዊና ማቴሪያሊስት አቀራረብ እጅግ በጣም የራቁና የሚቃረኑትም ዘዴዎች ናቸው:: የነገሩ እምብርት እንግዲህ ይህ ሆኖ ሳለ የኢትዮጵያ አብዮት በተቀየሰለት ፕሮግራም መሠረት ግቡን እንዲመታ ከተፈለገ፣ ፊውዳሳዊ ያስተሳሰብና ያሠራር ዘዴዎችን ለማሸነፍ መቻል ይኖርብናል:: ለዚህም ፍቱን የሚሆነው መድሃኒት የዲሞክራሲያዊ መብቶች ለሰፊው ሕዝብ መታወቅ ነው :: ያለነዚህ መብቶች ፣ ያለ ሰፊው ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ፣ በኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች መካከል ያሉትንና ወደፊትም እስከውህደታችን ድረስ ሊፈጠሩ የሚችሉትን ልዩነቶች ለመፍታት የማይቻል ነው ባይባልም እጅግ በጣም ብዙ ችግሮች ይኖራሉ፤ ረጅም ጊዜንም ይፈጃል::

2. ዕውነተኛ የልዩነት ነጥቦች

ባለፈው የካቲት ወር የጋራ መግለጫው ከመውጣቱ በኋላም ሆነ ከዚያ በፊት፣ በመኢሶንና ባንዳንዱ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች መካከል ዕውነተኛ የልዩነት ነጥብ ሆኖ የቆየው የብሔረሰቦች ጥያቄ ነው:: ከነዚህ ድርጅቶች ጋር በፕሮግራማችን ደረጃ ልዩነቶች አሉ:: ግን ይህ ብቻ ሳይሆን፣ በቲዎሪው ደረጃና እንደዚሁም በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጥያቄውን እንዴት መመልከት አለብን በሚለው ላይ ልዩነቶች አሉ:: ይሁንናም፣ እስከዛሬ ድረስ፣ ድርጅታችን ከማንኛውም ሌላ የኅብረቱ አባል ድርጅት ጋር የይፋ ክርክር በጽሑፍ አልጀመረም:: ለምን?

ድርጅታችን በብሔረሰብ ጥያቄ ላይ በተለይና በሌሎችም አንዳንድ ጥያቄዎች ላይ ባጠቃላይ የይፋ ክርክርን ያልጀመረው ፣ የኢትዮጵያ አብዮት አሁን በደረሰበት ደረጃ፣ ለአብዮቱ ወደፊት መግፋትና ለተራማጆች የተፋጠነ ኅብረት ሲባል፣ ከልዩነት ነጥቦች ይልቅ በስምምነት ነጥቦች ላይ ማተኮሩ ይበልጥ ስለሚጠቅምና እንደዚሁም አብዮቱ እየገፋ ሲሄድ የልዩነት ነጥቦቹ እየጠሩ ሊሄዱ ይችላሉ በሚል ነበር:: ይሁንናም የርስ በርስ ውይይቶችም ሆኑ የኅብረት ውይይቶች በተካሄዱበት ወቅት ሁሉ፣ ያለንን አስተያየት ለሌሎች ድርጅቶች ጓደኞቻችን ከመሰንዘር ፈጽሞ አልተቆጠብንም:: በጽሑፍ ክርክር ለመክፈት የመቆጠብ አቋማችንን ግን ሌሎቹ ከኛ ጋር ያስተሳሰብ ልዩነት ያላቸው ጓዶች የተረዱልን አይመስልም:: ስለሆነም፣ በኛ ግምት ስህተተኛ ናቸው የምንላቸውን ነጥቦች በሰፊው ማሰራጨታቸው ብቻ ሳይሆን፣ አንዳንዶቹን እንዲያውም ወደመንግሥት አቋም እስከመለወጥ ድረስ ደርሰዋል::

የብሔረሰቦች ጥያቄና ለርሱ የተሰጠው የሪጂናል አቶኖሚ መልስ ከነዚህ ዓይነት ነጥቦች ውስጥ አንዱ ነው:: በብሔረሰብ ጥያቄ ላይ የመኢሶን ፕሮግራም ይዘት በኛ አስተያየት ፍጹም ማርክሳዊ ሌኒናዊ በመሆኑ፣ የዚህን አስተያየት ተቃራኒ የሚያሰማነን ሰው ወይንም ድርጅት እስከመጨረሻው ድረስ በርሱ እንፀናለን:: ሪጂናል አቶኖሚን በመፈክርና በመፍትሔ ደረጃ የሚያቀርቡት ድርጅቶች አንዳንዴ የሚሉን፣ "የፕሮግራም አቋማችሁ ልክ ነው፤ ግን አሁኑኑ 'ተግባራዊ መፍትሔን' ማቅረብ አለባችሁ " ነው ከዚያም የራሳቸውን አቋም ትክክለኛነት ለማሳመን ሲፈልጉ፣ ስታሊን ሪጂናል አቶኖሚን መርጠአል፣ ሪጂናል አቶኖሚ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው ...ወዘተ ይላሉ::

በመሠረቱ ግን እንዲንከራከርበት ያስፈልጋል ከተባለ፣ ለአንድ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅት ፣ የብሔረሰቦችን መብት በገደብ የማወቅ ጉዳይ በፍጹም አብዮታዊ አይደለም:: ብሔረሰቦች የራሳቸውን እድል የመወሰን መብት አላቸው ማለት፣ ብሔረሰቦቹ ከፈለጉ ከአንዱ ከተወሰነ ግዛት ተገንጥለው የራሳቸው መንግሥት እስከማቋቋም ድረስ መብት አላቸው ማለት እንደሆነ ሌኒንና ስታሊን ደግመው ደጋግመው አስተምረዋል:: በዚያውም ግን ይህንን መብት ማወቅ ማለት ደግሞ ብሔሮች ወይንም ብሔረሰቦች ሁሉ ይገንጠሉ ማለት እንዳይደለም ያስተምሩናል:: እንዲያውም ይህንን መብት፣ ይህንን ምንም ገደብ ሊደረግበት የማይገባ መብትን በቅድሚያ ማወቅ በብሔሮች ወይንም በብሔረሰቦች መካከል ፍጹም እኩልነት እንዳለና በዚህም እኩልነት እንደሚታመን ስለሚያረጋግጥ፣ ባንድ በኩል ብሔረሰቦች ይበልጡን

አንድነትን እንዲጐ ያደርጋቸዋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የብሔረሰብን እንቅስቃሴዎች ከመሬት ከበርቴዎችና ከከበርቴዎችና ከሌሎችም አድሃሪ መደቦች ቁጥጥር ስር ያወጣቸዋል:: ስታሊን "ዲያሌክቲካዊ የምርምር አቀራረብ የሚያስፈልገው አንድ ነገር ቢኖር፣ እርሱም የብሔሮች ጥያቄ ነው" የሚለው እነዚህን መሠረታዊ የመነሻ ነጥቦች በማስታወስ ነው::

በዚህ በብሔረሰቦች ጥያቄ ላይ በሌላ ጊዜና ቦታ በሰፊው እንመለስበታለን እዚህ ላይ ግን ባሉን ልዩነቶች አንዳንድ ነጥቦችን ብቻ አንስተን እንለፍ::

አንደኛ፣ የብሔረሰቦች ጥያቄ፣ እንደሌሎች የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄዎች ሁሉ፣ ዕውነተኛና ዘላቂ መፍትሔውን ሊያገኝ የሚችለው የመንግሥት ሥልጣን በሰፊው ሕዝብ እጅ ሲገባ ብቻ ነው::

ሁለተኛ፣ ስታሊን ሪጂናል አቶኖሚን የሚመርጠው ባንድ ግዛት ውስጥ ለመቆየት በቅድሚያ ምርጫ ለሚያደርጉት ብሔሮች ወይንም ብሔረሰቦች ነው:: ማለትም መጀመሪያ የብሔሮች የመገንጠል መብት ይታወቅና ነው ወደመፍትሔው ሽግግር የሚደረገው:: ደግሞም መፍትሔው አንድ ብቻ፣ ለምሳሌ ሪጂናል አቶኖሚ ብቻ፣ ሳይሆን ሌሎችም አሉ:: ዋናው ቁም ነገር ግን የያንዳንዱ ብሔር ወይንም ብሔረሰብ የፈለገውን ዓይነት መፍትሔ ለመምረጥ የመቻል መብቱ መታወቅ ነው::

ሶስተኛ፣ ስታሊን ደጋግሞ እንደሚያስተምረን ሁሉ፣ የብሔሮችን ጥያቄ በሚመለከተው በኩል ሁልጊዜ ከተጨባጩ የታሪክ ሁኔታ መነሳት አለብን እንጂ እንደዚሁ "ተግባራዊ መፍትሔን ማቅረብ አለብን" በሚል፣ በራስ ላይ ሰው ሰራሽ በሆነ መንገድ በተጫነ ግዴታ ይህንን ወይም ያንን "መፍትሔ" ለማቅረብ መጣደፍ የለብንም:: የኢትዮጵያን ታሪክና ኅብረተሰቧ ያሉበትን ደረጃ በትክክል ብናጤን፣ ይህቺ አገር ከዛሪስት ሩሲያ ቢበልጥ እንጂ ባላነሰ መንገድ "የብሔረሰቦች እስር ቤት" ሆና እንደኖረች እንረዳለን:: በኢትዮጵያ ጭቁን ብሔረሰቦች ላይ በፊውዳሉ ሥርዓት የተፈጸሙት ግፎች እጅግ በጣም አስቃቂ ስለነበሩ፣ ዛሬም ቢሆን በጨቋኙና በተጨቋኝ ብሔረሰቦች መካከል ብዙ ቂም፣ ጥርጣሬና ጥላቻ አለ:: በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ቅስቀሳቸውን ማተኮር ያለባቸው በብሔረሰቦች ሙሉ የእኩልነት መብቶች ላይ ነው:: ስለዚህም ነው መኢሶን "ተግባራዊ መፍትሔ" የሚባለውን ነገር እንደሁኔታውና፣ እንደጊዜው፣ እንደመፍትሔ ጠያቂው <u>ብሔረሰብ</u> አይቶ መወሰንን የሚመርጠውና ባሁኑ ወቅት ይበልጡን በእኩልነትና በአንድነት ላይ ቅስቀሳውን የሚያተኩረው::

የኤርትራን ጥያቄ በሚመለከተው በኩል፣ መኢሶን የክፍለጠገሩን ከኢትዮጵያ ባሁኑ ወቅት መገንጠል እንደሚቃወም ደጋግሞ በየጽሑፉ አቋም ቢወስድም ፣ደግሞም በተለይ የግንቦት ስምንቱን የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የፖሊሲ ውሳኔ በሙሉ ልብ ደግፍ መግለጫ ቢያወጣም ፣አንዳንድ ድርጅቶችና ግለሰቦች ፣መኢሶን የኤርትራን መገንጠል ይደግፋል በማለት በያካባቢው የሐሰት ዘመቻን አካሂደውብናል:: በኤርትራ ጥያቄ ላይ አሁንም ቢሆን መኢሶን የግንቦት ስምንትን የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን የፖሊሲ ውሳኔ በመደገፍ፣ ችግሩ ሰላማዊ መፍትሔን እንዲያገኝ ጠይቃል:: በርግጥ ባሁኑ ወቅት የኤርትራ ተገንጣይ ድርጅቶች በተለያዩ ደረጃዎች የኢምፔሪያሊዝምና የአረብ አድሃሪ መንግሥታት መሣሪያዎች ሆነው አብዮቱን ለመቀልበስ ከሚፈልጉ አድሃሪዎች ጋር ተሰልፈዋል : ይሁንና ሰፊው የኤርትራ ሕዝብ መገንጠልን አይፈልግም:: ስለዚህም፣ ባሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ባለው ትግል ውስጥ፣ የኤርትራን ሰፊ ሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት መታገል፣ በተቻለ መጠን ይህ ሕዝብ እስከዛሬ በተቀበለው ስቃይ ላይ አሁንም እንደገና እንዳይመታ መጠንቀቅ፣ በተገንጣይ ድርጅቶች መካከል ያሉትን ቅራኔዎች በመጠቀም እነርሱን ብቸኛ ማድረግ፣ በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ካሉት ተራማጆች ጋር ውይይትን ለመክፈት መጣጣርና አድሃሪዎቹን ደግሞ በኃይል መምታት ያስፈልጋል::

ባለፈው የካቲት ወር የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች የጋራ መግለጫ በወጣበት ወቅት፣ በኛና ባንዳንድ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች መካከል የነበረ እውነተኛ የልዩነት ነጥብ የብሔረሰብ ጥያቄ ብቻ ነበር ለማለት ይቻላል:: የኢትዮጵያ አብዮት በጣም ፈጣን ነው ተብሎአልና፣ ካለፈው ግንቦት ወር ወዲህ ደግሞ ሌሎች የልዩነት ነጥቦች ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩ ይመስላል:: "ቢሮክራሲ ይውደም"፣ "የነቃ የተደራጀ፣ የታጠቀ የሰፊው ሕዝብ አመጽ ያሸንፋል" በለን ከዓመት በላይ ሁላችንም አንግበናቸው የቆየን መፈክሮች ወደልዩነት ነጥብነት እየተለወጡ የሄዱ ይመስላል:: ይሁንናም፣እነዚህ ገና ባጥቁርና ነጭ የመጨረሻ መልካቸውን ይዘው አልመጡምና እነርሱን ለጊዜው ወደጐን ትተን፣ በዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ በመካሄድ ላይ የሚገኙትን ክርክሮች መመልከቱ ይጠቅማል:: እዚህ ላይ ፣ ከጋራ መግለጫው ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ እንደገና ተመልሶአንባቢው እንዲያጤነው እንጋብዛለን::

መግለጫው "ባስቸኳይ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ መታወጅ አለባቸው" ይላል የእነዚህ መብቶች መታወጅ ለምን እንደሚያስፈልግ ምክንያቶች ሲሰጥም 1. "በስውር ታፍነው የሚሠሩ ተራማጅ ድርጅቶች" አብዮቱን ለመቀልበስ ያሰፈሰፉትን አድሃሪያን በይበልጥ ለመቋቋም እንዲችሉ፣ 2. ትግላቸውን በይፋ ለማካሄድ እንዲችሉ 3. ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎችንና ሰፋፊ ድርጅቶችን ለማቋቋም እንዲችሉ ነው ይላል : ከመርሃግብሩ 13 ነጥቦችም ሁለተኛው "ይህንን የሰፊውን ሕዝብ መንቃትና በየፈርጁና በየደረጃው መደራጀት ለማገዝ አስፈላጊ የሆኑት ዲሞክራሲያዊ መብቶች ባስቸኳይ እንዲለቀቁ በኅብረት መታገል::"

ብሎአል:: "ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ" የሚለውን መፈክር ቢያንስ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ሁሉም ድርጅት ሲያስተጋቡ ቆይቷል::ዛሬ ግን አንዳንዶቹን ድርጅቶች ይህ መፈክር በልዩ ልዩ ምክንያቶች ይህ መፈክር ይቀፋቸው ጀምሯል:: ለምሳሌ የወዛደር ሊግ ለባን ወዝ ሰኔ 17 ቀን ባወጣው 32ኛው ቁጥሩ፣"ያለገደብ":የሚለው ሐረግ አሁንም ቢሆን አሻሚና የዴሞክራሲን ትርጉም የሚጻረር ጽንሰ ሃሳብን ያዘለ"እና መፈክሩ "የዴሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች" በሚለው ይተካ የሚል ሃሳብ አቅርቦአል:: በገደብ ያለገደብ፣ ለምን ለማን፣ የሚለው ክርክር ባለፈው ዓመት ለጥቂት ወራት ዴሞክራሲ ሰፍኖ በነበረበት ወቅት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ብዙ ተተችቶበት ያለቀለት ነገር መሆኑን ስናስታውስ፣ ሊግ አሁን ይህንን ጥያቄ ማንሳቱ ባጠቃላይ ስለዴሞክራሲያዊ መብቶች ጉዳይ የመንፈስ ጭንቀት መኖሩን ከማሳየቱ በስተቀር ፣ በውነቱ በክርክሩ ላይ የሚጨምረው ምንም አዲስ ነገር የለም:: ይህ ያለቀለት ክርክር ከዓመት በኋላ ዛሬ እንዴት ተነሳ?

ግን ከዚህም ይበልጥ የሚያሳስበው ስለመብቶች መለቀቅ ጉዳይ ይህ የወዝ ቁጥር የሚሰነዝረው አስተያየት ነው:: በሰፊው እንጠቅሳለን::—

"የዴሞክራሲ መብቶች ጭቁኖችን ለወሳኝ ፍልሚያ በከፍተኛ ደረጃ እንዲዘጋጁ በር ከፋች ናቸው :: ይሁን እንጂ ጭቁኖች ዴሞክራሲያዊ መብቶች በብቸኝነት ለደህንነታቸው ሊጠቀሙበት የሚችሉት አንድ ማእከል ሲኖራቸው ነው:: ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ይህ የግራው ክፍል ማእከል የሚገኘው የተራማጆች ኅብረት በውይይትና በትግል ተፈጥሮ በመጠናከር ወደውህደት ሲያመራ ብቻ ነው::..."

ወዝ ቁጥር 32ን ጓደኞች ሁሉ ፈልገው ማንበብ አለባቸው፣ ማጥናት አለባቸው:: ስለዴሞክራሲ ብቻ ሳይሆን ስለሌሎችም ነጥቦች በጣም ጠቃሚ የሆኑ ፣ግን ደግሞ ይህን ያህልም ግልጽ ባልሆነ ቋንቋ ያልተሰነዘሩ አስተያየቶች አሉበት:: ስለሆነም፣ ይህኛው ቁጥር ከሌሎች የወዝ ቁጥሮች ለየት ያለ ሆኖ አግኝተነዋልና ይጠና:: ዴሞክራሲን በሚመለከተው በኩል ከዚህ በላይ የቀረበው ጥቅስ፣ እንደገባን ከሆነ፣ የሊግ አስተሳሰብ፣ በቀላል አማርኛ ፣የወዛደሩ ፓርቲ ካልተፈጠረ፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሊለቀቁ አይገባም ነው:: ምክንያቱም "አንድ ማእከል" መኖር ስላለበትና ይህም "የሚገኘው የተራማጆች ኅብረት በውይይትና በትግል ተፈጥሮ በመጠናከር ወደውህደት ሲያመራ ብቻ" ነውና! ውህደት ማለት የወዛደር ፓርቲ መፈጠር ማለት ነው:: የለም የወዛደሩ ፓርቲ ካልተፈጠረ ማለታችን ሳይሆን ፣ወደውህደት "ስናመራ" ማለታችን ነው እንዳይባል፣ ዛሬም ፣በሐምሌ ወር 1969፣ወደዚያው "በማምራት"ላይ እንደሆንን ነው የሚገባን::በዚህ ሁኔታ እንግዲህ መቼ ነው የተራማጆች ኅብረት ተጠናክሮ "ወደውህደት አመራ" የሚባለው? ማን ይወስንልናል?

ግን ደግሞ ሌላ የጥቅሱ ነጥብ አለ:: ይኸውም የተራማጆች ኅብረት "በውይይትና በትግል መጠናከር" ነው:: ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሌሉበት ሁኔታ ምን ዓይነት ውይይትና ትግል ነው ሊኖር የሚችለው? ወይንስ ውይይቱና ትግሉ ባሁኑ ወቅት በኅብረት ኮሚቴው ፣ ማለትም በ15 ሰዎች መካከል፣ ባንድ ጠረጴዛ ዙሪያ የሚካሄደውን ማለት ነው? መኢሶን በተለያዩ የልሳኑ ቁጥሮች ደጋግሞ እንደገለጸው ሁሉ ፣የተራማጆችን ኅብረት ለማጠናከር፣ የወዛደሩን ፓርቲ ለመገንባት፣ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩን ለመመሥረትና በጠቅላላውም አብዮቱ ወደፊት ገፍቶ ግቡን እንዲመታ ለማድረግ፣ እነዚህ መብቶች የግድ ባስቸኳይ ያስፈልጋሉ:: ስለሆነም፣ የሊግ ጓደኞችና የኛ አቀራረብ ፍጹም ተቃራኒያች ሆነው እናገኛቸዋለን::እነርሱ የሚሉት የወዛደሩን ፓርቲ ፈጥረን ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይምጡ ሲሆን፣ እኛ ደግሞ የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያስፈልጋሉ ነው:: እንደሚባለው የመኢሶን "ፍልስፍና" የሚመሠረተው አብዮትን የሚሠራው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠረው ሰፊው ሕዝብ እንጂ ጥቂት ግለሰቦች ወይንም ቡድኖች አይደሉም በሚለው ላይ ነው::

በዚህ በወዝ 32 ጥቅስ ላይ ሌሎችንም ትችቶች ለማቅረብ ይቻል ነበር:: እነርሱን ለአንባቢ እንተውና ወደመግለጫው ጥቅስ እንመለስ::

መግለጫው ለዴሞክራሲያዊ መብቶች ባስቸኳይ መታወጅ አስፈላጊነት የሚሰጠው የመጀመሪያው ምክንያት፣ "በአሁኑ ወቅት አብዮቱን ለመቀልበስ ያሰፈሰፉትን አድሃሪያን በይበልጥ ለመቋቋም" እንዲቻል ነው ይላል:: ማንም ተመልካች በግልጽ እንደሚያየው ሁሉ፣ ከየካቲት ወር ወዲህ፣ የተባሉት አድሃሪያን ይበልጥ፣ አሥር እጅ ይበልጥ፣ "አሰፈሰፉ" እንጂ በምንም መንገድ ፀረአብዮት ትግላቸውን አልቀነሱትም:: በመግለጫው ትክክለኛ አስተያየት ተመርኩዞ ከተሄደ፣ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ዛሬ አስፈላጊ ናቸው ተብሎ ታምኖበት እርምጃም ሊወሰድ ሲገባው ፣በአንዳንድ አካባቢያች ለዴሞክራሲያዊ መብቶች ባሁኑ ወቅት አለማስፈለግ እንዲያውም ያድሃሪያች መጠናከርና "ማሰፍሰፍ" አንድ ምክንያት ሆኖ ይቀርብ ጀምሮአል! የተገላቢጦሽ ነገሮች ሄደት በግልጽ የሚታይና የዛሬ ስድስት ወር የተባለውንም በተገላቢጦሽ መንገድ እንደሚያረጋግጥ ባይኖቻችን እያየን፣ ያን ጊዜ ለአንድ ዓላማ የተሰጡት ምክንያቶች ዛሬ ለምን ለተቃራኒው ዓላማ እንደሚቀርቡ ግራ የሚያጋባ ነው! በኛ በኩል አሁንም የምንለው፣ ሰፊው ሕዝብ ጠላቶቹን ይበልጥ ለመቋቋም እንዲችል ይበልጥ መንቃት፣ ይበልጥ መደራጀት፣ይበልጥ መታጠቅ አለበት ነው:: ለዚህም ደግሞ የዴሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ ሊታለፍ የማይቻል አስፈላጊ ነገር ነው::

በመግለጫው ውስጥ "በስውር ታፍነው የሚሠሩ ተራማጅ ድርጅቶች" ስለተባለው፣

አንዳንድ የኅብረት ኮሚቴው አባላት፣ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ቢፈቀዱም እንኳን፣ እነዚህ ሕቡእ ድርጅቶች በይፋ መውጣት የለባቸውም!" የሚል ዓይነት አስቂኝ ምክንያት እየተሰጠ ነው:: እዚህ ላይ ማስታወስ የሚያስፈልገን ቁምነገር አለ:: ይኸውም መኢሶን ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚጠይቀው ይህን ያህልም ለራሱና ለሕቡእ ድርጅቶች ሳይሆን፣ ለሰፊው ጭቁን ሕዝብ ነው:: ይህ ሕዝብ የንግግርን፣ የጽሑፍን፣ የመሰብሰብን፣ የመደራጀትን መብቶች እስካላገኘ ድረስ በፍጥነት ሊነቃና ሊደራጅ አይችልም:: በርግጥ ለሰፊው ሕዝብ አሁንም ቢሆን እነዚህ መብቶች አሉ ይባላል:: የአርሶአደር፣ የወዛደርና የሌሎችም ሠርቶአደሮች ማህበራት አሉ፤ በፈለጋቸው ጊዜ ይሰበሰባሉ፤ የፈለጋቸውን ይናገራሉ፣..ወዘተ ይባላል:: ግን ይህ አሁን ያለውን ጭብጥ ሁኔታ አጋንኖ ባሸበረቀ ቀለማት ሸፋፍኖ ማቅረብ ነው:: ሰፊው ሕዝብ አሁንም ቢሆን፣ በከተማም ሆነ በገጠር፣ በፊውዴ ቡርዧው የመንግሥት አውታሮች ተወጥሮ ተይዞአል፤ ከቢሮክራሲውም ጋር ኃይለኛ ትግል እያካሄደ ነው:: ሰፊው ሕዝብ የገዛ እድሉን በገዛ እጁ ጨብጦአል ከሚባልበት ደረጃ አሁንም ገና በጣም ሩቅ ይገኛል:: ስለሆነም፣ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የሰፊው ሕዝብ አጋር እስከሆነ ድረስ ሰፊውን ሕዝብ ወደዚያ ደረጃ የሚያቀርቡትን እርምጃዎች ሁሉ በወቅቱ የመውሰድ ኃላፊነት ስላለበት፣ ይህ መንግሥት በሰፊው ሕዝብ እምነት እስከኖረው ድረስ፣ በኛ አስተያየት ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እንዲለቀቁ የማድረግ አብዮታዊ ግዴታ አለበት እንላለን!::

እንግዲህ ለማጠቃለል ያህል፣ በዚህ ነጥብ ላይ ብዙ ጠተታያችን ሳንጨምር፣ ባሁኑ ጊዜ በመኢሶንና በሌሎች የኅብረት አባል ድርጅቶች መካከል አንድ የቆየ ልዩነትና አሁን ደግሞ አንድ ሌላ እየጐላ የሚሄድ ልዩነት እንዳሉ እንገነዘባለን:: በጋራ መግለጫው - ውስጥም ሆነ በየድርጅቱ ልሳን ውስጥ፣ ኅብረቱን ለማጠንከር ዲሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካና የርዕዮተዓለም ትግልን ማካሄድ እንዳለብን ተደጋግሞ ተገልጦአል:: ስለዚህም፣ ካሁን ጀምሮ እነዚህን የልዩነት ነጥቦች ለውይይት ማቅረቡ ይጠቅማል ብለን እንገምታለን:: ደግሞም በኅብረት ኮሚቴው የፀደቀው የኅብረቱ መተዳደሪያ ደንብ ለዚህ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል::

፫. ስለኅብረቱ የድርጊት ኘሮግራም

የብሔረሰቦችን ጥያቄ፣ የዲሞክራሲ ጥያቄ፣ የማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች መቀራረብ፣ መተባበርና ተዋሕዶ ፓርቲን መፍጠር፣ እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች የተያያዙ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም በአንድ መሠረት ላይ የቆሙ ነገሮች ናቸው:: በብሔረሰቦች ከብረት የጠነከረ የጭቁን መደቦች አንድነት እንዲመሠርቱና በመካከላቸው ለብዙ ዘመናት የኖረውን ጥላቻና የርስ በርስ ጥርጣሬ እንዲርገዱ የብሔረሰቦችን የእኩልነት መብት ማወቅ ያስፈልጋል: ተራማጆች በጠቅ እንዲተባበሩ፣ በመካከላቸው ያሉት አለመተማመንና ሽኩቻዎች ጠፍተው ያስተሳሰብና የድርጊት አንድነትን ገንብተው እውነተኛ የወዛደሩን ፓርቲ እንዲፈጥሩ ከተፈለገ፣ ዲሞክራሲያዊና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት በመካከላቸው መፈጠር ይኖርበታል:: ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሌሉበትና የየካቲቱ መግለጫ እንዳለው ሁሉ ድርጅቶቹ "ታፍነው" በሚሠሩበት ባሁኑ ሁኔታ ግን ይህ እኩልነት አለ ለማለት ፈጽሞ አያስደፍርም:: እኩልነት የለም ስንልም አንዱ ድርጅት በአባል ብዛት ወይንም በስፋት ከሌላው ይበልጣል ለማለት ሳይሆን፣ አንዱ ወይም ሌላው ድርጅት እንደየሁኔታው በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በኩል ከሌሎቹ የበለጠ ተደማጭነትን ለማግኘት የሚችልበት ሁኔታ አለ ለማለት ያህል ነው:: ስለዚህም ነው ሃቀኛና ዲሞክራሲያዊ አሰራር ይኑር የምንለው::

እስከዚያው ድረስ ግን፣ አብዮታውያን ባንድ በኩል ባንድ በተወሰነ ወቅት የኃይሎችን አሰላለፍ አጢኖና በዚያም ላይ የራስን ድርጊት የመቀየስ ግዴታ ስላለባቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ ሁኔታ በሚያበረክተው እድል ትንሽም ብትሆን መጠቀም ስላለባቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ ሁኔታ በሚያበረክተው እድል ትንሽም ብትሆን መጠቀምም ስላለባቸው፣ ባሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ በጅግ አስፈላጊ የሆነውን የተራማጆችን ሕብረት ለማጠናከርና አብዮቱ ወደፊት እንዲራመድ ለማድረግ እንታገላለን:: ከዚህ ጋር የተያያዘውን የድርጊት ኘሮግራም የምንቀበለውና የመኢሶን ጓዶችና ደጋፊዎች ሁሉ እንዲታገሉለት ጥሪ የምናቀርብላቸውም በዚሁ ምክንያት ነው:: እንደዚሁም ጓዶች ሁሉ በየካቲት ወር የወጣውን የጋራ መግለጫና መርሃግብር እንደገና እንዲያጠኑትና ከሥራ ላይ እንዲያውሉት እንጠይቃለን:: እንደዚሁም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ኘሮግራም!! እንደዚሁም የመኢሶንን ኘሮግራም!!

አንባቢ ይህንን ድርደራ ተመልክቶ "የኢትዮጵያ አብዮት በውነቱ በኘሮግራም እጦት አልተቸገረም!" ሳይል አይቀርም:: በኛ አስተያየት ኅብረትም ቢሆን በኘሮግራም እጦት አልተቸገረም: ለመሥራት ከተፈለገ፣ በርግጥና በሃቅ ሁሉም ድርጅት ለኅብረት፣ ከዚያም ለውህደትና ለወዛደሩ ፓርቲ መፈጠር የሚታገል ቢሆንማ ኖሮ የየካቲቱ መርሃ ግብር እራሱ በበቂ ነበር:: የድርጊት ኘሮግራምን ማውጣት በራሱ ለመሥራት ያለንን ፍላጐትና ችሎታ አይጨምርልንም:: ይሁንናም፣ መኢሶን ይኸንን የድርጊት ኘሮግራም ሃላፊነት በተሞላበት መንፈስ ይቀበላል፤ አባሎቹና ደጋፊዎቹም ሁሉ እንዲያጠኑትና ይዘቱንም ከሥራ

ላይ እንዲያውሉት ይጠይቃል::

ማንም በቀላሉና ባንድ ጊዜ ለማየት እንደሚቻል ሁሉ፣ ከዚህ የድርጊት ፕሮግራም ውስጥ ባለመኖሩ ብቻ እንኳን የተለየ አትኩሮትን የሚጠይቀው የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጉዳይ ነው:: በርሱ ፈንታ፣ ፕሮግራሙ

"ለትግሉና ለሽግግሩ ይበልጥ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን መሠረት በማድረግ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ለሕብረቱ፣ ላሉትና ወደፊትም ለሚፈጠሩት ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች፣ ለተራማጅ ድርጅቶችና ለፀረ ፊውዳል፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ኃይሎች የማቴሪያልና የሞራል ድጋፍ እንዲሰጥ መታገል፣" ይላል::

መኢሶን በበኩሉ በውይይቱ ላይ የጠየቀው ሌላው ቢቀር ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች እንዲታወቁ መታገል የሚለው የመርሃ ግብሩ ነጥብ ቢያንስ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ እንዲገባ ነበር:: ይህ ተቀባይነትን ሊያገኝ አልቻለም::

ይሁን እንጂ፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ይህው የድርጊት ፕሮግራም በአምስተኛ፣ በስድስተኛና በሰባተኛ ነጥቦች የሚያቀርባቸው ተግባሮች በርግጥ ከሥራ ላይ እንዲውሉ፣ አብዮቱም ባጠቃላይ ወደፊት እንዲጓዝ ለማድረግ ከተፈለገ፣ የሰፊው ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ፣ማለትም መብቶች ያስፈልጋሉ::...ሁሉም ዝርዝር ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው::

መኢሶን ይህንን የድርጊት ፕሮግራም ስለሚያምንበት ብቻ ሳይሆን ፣ በሕብረቱ ደንብም መሠረት፣ በነጥቦቹ ላይ ልዩነቶች ቢኖሩትም፣ ፕሮግራሙን ከሥራ ላይ የማዋል ግዴታ አለበት:: የኅብረቱ ደንብ በሕብረት ኮሚቴው 29ኛ ስብሰባ ላይ ሐምሌ 11 ቀን 1969 ፀድቋል::

በኛ አስተያየት፣ እንደየጋራ መግለጫው ሁሉ፣ ይህም ደንብ በኢትዮጵያ አብዮት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታን ይይዛል:: ደንቡ ዲሞክራሲያዊ ነው:: አብዮታዊ ነው:: ለአባል ድርጅቶቹ የሚሰጠው መብትና ግዴታ ትክክለኛና ከጊዜው ሁኔታ ጋር የሚሄዱ ናቸው:: የያንዳንዱ ድርጅት ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚያውም ግን በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ ብዙ ተግባሮችን በሕብረት ለማከናወን እንደሚቻል የሚያበስር ደንብ ነው:: ይሁንናም፣ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የሕብረቱ ችግሮች ሁሉ ምክንያት፣ ይህ ደንብ እንደኃይለሥላሴ ሕገመንግሥት ሁሉ፣ የወረቀት ጉዳይ ሆኖ እንዳይቀር ያንዳንዱ ድርጅት መቻከል አለበት:: መኢሶን ለደጋፊዎቹና በጠቅላላው ለሰፊው ሕዝብ የሚያደርገው ጥሪ፣ ደንቡን በሚገባ እንዲያጠኑትና በትክክል ከሥራ ላይ መዋል አለመዋሉንም እንዲከታተሉ ነው:: በድርጅታችን በኩል ይህ ደንብ በትክክል ከሥራ ላይ እንዲውል እስከመጨረሻው ለመታገል ቃል እንገባለን::

የተፈጠረውን ሕብረት በሚመለከተው በኩል፣ መኢሶን በተቻለው መንገድ ሁሉ ሕብረቱ በሀቅና በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንዲሠራና እንዲጠነክር ጥረት ያደርጋል::ምንም እንኳን በድርጅታችን ላይ "መኢሶን አብጦ እራሱ ፓርቲ ለመሆን ይፈልጋል፤ መኢሶን በሕብረት አያምንም፣ መኢሶንን የጠባብ ቡድን ስሜት ያጠቃዋል ....ወዘተ" የሚሉ ዘመቻዎች ተደጋግመው ቢካሄዱበትም፣ መኢሶን ሕብረትን ይፈልጋል::የዛሬ ሰባት ወር በሰፊው ሕዝብ ድምፅ፣ ቁጥር 42 ፣ ሌኒንን በመጥቀስ እንደገለጸነው ሁሉ፣እንኳንስ ለአብዮቱ እስከአሁን ይህን ያህል አስተዋጽኦ ካደረጉ ድርጅቶች ጋር ይቅርና፣"ከማይታመኑ ሰዎች ጋርም እንኳን ቢሆን ጊዜያዊ ሕብረትን መፍጠር የሚፈሩ በራሳቸው የማይተማመኑ ብቻ ናቸው::የዚህ ዓይነቶቹን ሕብረቶች ሳይፈጥር ሊኖር የሚችል አንድም የፖለቲካ ፓርቲ የለም::" ለመቀራረብ ፣ለመተማመን፣ አብሮ ለመታገልና በዚህም ሂደት ያስተሳሰብና የድርጊት አንድነትን ፈጥሮ የኢትዮጵያን የወዛደር ፓርቲ ለማቋቋም የዚህ ዓይነቱ ሕብረት እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን መኢሶን ያምናል:: እያንዳንዱ የሕብረት አባል ድርጅት ወይንም የየድርጅቱ ግለሰብ አባሎች ሕብረቱን ለልዩ ልዩ የቅርብ ጊዜና የረጅም ጊዜ ዓላማዎች ሊፈልጉት ይችላሉ፤ መኢሶን ግን ሕብረቱን የሚፈልገው የኢትዮጵያ አብዮታውያን እንዲዋሃዱና የወዛደሩን ፓርቲ ፈጥረው፣ በዚህም ፓርቲ አማካይነት ሰፊውን ሕዝብ ከዳር እስከዳር አንቀሳቅሰው አብዮቱን ከግቡ ለማድረስ እንዲታገሉ ለማድረግ ብቻ እንደሆነ እንዲታወቅልን እንወዳለን::

ሕብረቱ በራሱ ግን የሚፈለገው ለዚህ ለረጅም ጊዜ ዓላማ ብቻ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያ ዛሬ ለገባችበትም ውጥረት ሊያስወጣት የሚችል መሣሪያ ስለሆነ ነው:: በርግጥም ደግሞ ይህ ውጥረት ሊወገድ የሚችለው የሰፊው ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ ሲገኝ ነው ከተባለ፣ ይህንን ሰፊ ሕዝብ ለመቀስቀስና ባአብዮቱ ጠላቶችና ችግሮች ላይ እንዲሰለፍ ለማድረግ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ታጋዮች ያስፈልጋሉ:: ይህንን ሁሉ ታጋይ ደግሞ እንኳንስ አንድ ሕቡእ ድርጅት ለብቻው ሊያሰልፍ ቀርቶ፣ ያሉት ድርጅቶች ሁሉ ተባብረውም እንኳን ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊያሰልፉ እንደማይችሉ ለማንም ግልጽ ይመስለናል::

ስለዚህም፣የኢትዮጵያ አብዮት ባሁኑ ወቅት ከኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች ሕብረት ከፍተኛ ኃላፊነትን ይጠይቃል:: ይህንን ሀላፊነት በሚገባ ለመወጣት የሚቻለው ፣ በሀቅና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ፣ እያንዳንዱ አባል ድርጅትም ሆነ ሕብረቱ የሕብረቱን ደንብ፣ የጋራ መግለጫውንና መርሃግብሩን፣ እንደዚሁም ከዚህ ጋር የተያያዘውን የድርጊት ፕሮግራም በትክክልና በሀቅ ከሥራ ላይ ለማዋል ሲታገሉ ብቻ ነው::

ያለበለዚያ ግን፣ በልዩ ልዩ ምክንያቶች፣ አንዱ ድርጅት ወይም ሌላው የተወሰነውን ነገር ከሥራ ላይ የማያውለው ከሆነ፣ ወይንም የሕብረቱን ውሳኔዎች ወደጐን ትቶ በበኩሉ የሚታየውን የሚያደርግ ከሆነ፣ ወይንም ደግሞ ከመጀመሪያውም ውሳኔዎቹ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የተደረሰባቸው እንዳይሆኑ ከተደረገ፣ ሕብረቱም የወረቀት ሕብረት ብቻ ይሆናል::

ከዚህ በፊት በየጽሑፎቻችን ደጋግመን እንደገለጽነው ሁሉ፣ መኢሶን ገና ለጋ ድርጅት ነው:: አንዳንዶች እንደሚሉት እራሱ "አብጦ" ወይንም ሌሎችን "ውጦ" ወደዐዘደር ጋር ቲነት ለመለወጥ ምንም ምኞት እንደሌለው እንደገና በዚህ አጋጣሚ ለማረጋገጥ እንወዳለን:: ድርጅታችን እንደሌሎቹ ድርጅቶች ሁሉ ገና የሚያድግና የሚበስል ድርጅት እንጂ የረጅም ዘመናት ታሪክና የትግል ልምድ ያለው ድርጅት አይደለም:: መኢሶን የሳይንሳዊ አመለካከትና ያሠራር ዘዴ ቀኖናዎች የለውም:: እንደማንኛውም ድርጅት ከትግሉና ከሌሎችም ያገርና ዓለምአቀፍ የወዛደር ድርጅቶች ለመማር ዝግጁ የሆነ ድርጅት ነው:: እንደማንኛውም ድርጅት ደግሞ ለራሱ በቀየሰው የፖለቲካ መስመር ያምንበታል፤ ለመስመሩ ይታገላል:: የሚያደርጋቸው ስህተቶች ሲኖሩም ወይም የያዘውን መስመር ልክ አይደለም. ከተባለ፣ እነዚህ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ፣ በሀቅና በጓዳዊ መንፈስ ተገልጸውለት እንዲያምንባቸው ቢደረግ እንደሚታረም የድርጅቱ የራሱ የውስጥ ትግሎች ያረጋግጣሉ::

ከመስከረም 69 ወዲህ በተካሄደው ኃይለኛ የመደብ ትግል ውስጥ፣ የመኢሶንን መስመር በመደገፍና ለአብዮቱ በመከላከል፣ በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ሥራ፣ በቀበሌ ማህበራት፣ በገጠር ከኢዲዩና ከሶማሌያ ሰርጎገቦች ጋር በመፋጋት፣ በርከት ያሉ ጓደኞቻችን የሕይወታቸውን ከፍተኛ መስዋእትነት አድርገዋል:: የነዚህን ፍጹም አብዮታዊ ጓደኞቻችንን አርማ ይዘን ለሰፊው ሕዝብ የነፃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ትግል እስከመጨረሻው ድረስ እንታገላለን:: የጠየቀውን መስዋእት ቢጠይቅም፣ የፈለገው የአብዮታዊ ጓደኞቻችን ቁጥር በጠላት ጥይት ቢወድቅም፣ ችግርንና ሞትን ሳንፈራ ወደፊት እንራመዳለን::ምኞታችን ለሰፊው ሕዝብ ትግል፣ ለአብዮቱ፣ ለነፃና ኩሩ ኢትዮጵያ ታግለን መስዋት ብቻ ነው:: እንግዲህ መስመራችን ይህ እስከሆነ ድረስ ከኢትዮጵያ ህቁና ተራማጆች ሁሉ ጋር የማንግባባበትና የማንዋሃድበት ምክንያት ስለሌለ፣ሕብረቱን እናጠናክር እንላቸዋለን::

ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ
ባስቸኳይ!!
የማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ሕብረት
ይጠንክር!!
የነፃ፣ የተደራጀና የታጠቀ የሰፊው ሕዝብ
አመጽ ያሸንፋል!!

<u>ማስታወሻ</u>:—

ይህ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ እንዳለቀ፣ የሶማሌያ ጦር ውጋዴንን ወረረ ተነገረ:: በጽሑፉ ላይ ለመጨመር የሚቻለው የተጠቀሱትን ተግባሮች በጥድፊያ ከሥራ ላይ እናውል የሚል ማሳሰቢያ ብቻ ነው::